DMU

Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 9(2025) 2134-2151

AJIDS

Journal homepage: www.ajids.dmu.edu.et

Volume 9(1), June 2025

# ትዳርን አስመልክቶ የሚነገሩ ቀልዶች ይዘት ትንተና

አስቴር ሙሉ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ሒውማኒቲስ ፋኩሊቲ፣ፎክሎር ትምህርት ክፍል

Corresponding author email: hewanmikb@gmail.com

**አጠቃሎ**

*ትዳር የሰው ልጅ ህልውናውን ለማስቀጠል ከሚያከናውናቸው ድርጊቶቹ ውስጥ አንዱ ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ትዳርን አስመልክቶ የሚነገሩ ቀልዶችን ይዘት መመርመር ነው። በዋናው ዓላማ ስር በቀልዶች አማካኝነት ትዳር እንዴት ተገልፆአል? ቀልዶች የትዳር እሴቶችን እንዴት አቅርበዋቸዋል? ቀልዶች በትዳር ውስጥ የስነፆታን ሚና እንዴት ገልፀዋቸዋል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል። ጥናቱ መደረጉ በማህበራዊ እሴቶች መጥበቅና (ወይም) መላላት ሂደት ውስጥ የትዳርን ሚና ለአንባቢ ይጠቁማል፣ ተጠኝው ማሕበረሰብ ያለበትን ማህበራዊ ቅርፅ እና እየሄደበት ያለውን መጪ ጊዜ ለአንባቢ ይጠቁማል፤ በቤተሰብና ማህበረሰብ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ ይሆናል፤ በቤተሰብና ማህበረሰብ ዙሪያ ለሚሰሩ ተቋማት የትኩረት አቅጣጫዎችን ያመላክታል። ጥናቱ ዓይነታዊ ነው። መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች በቃለመጠይቅና በንባብ ተሰብስበዋል። ጥሬ መረጃዎችና መረጃ አቀባዮች በአመቺ እና ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። ጥናቱ ከቦታ አንፃር መረጃ መረብንና ባህር ዳር ከተማን፣ ከጊዜ አንፃር አሁን በመከወን ላይ ያሉ ቀልዶችን፤ከቋንቋ አንፃር አማርኛ ላይ ወሰኑን አድርጓል። የተሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ከተመረመሩ በኋላ የዓላማ ጥያቄዎችን በሚመልስ መልክ ተመድበው በመዋቅራዊና "ሒውመር" ንድፈ ሀሳቦች ተተንትነዋል። ከትንታኔውም ቀልዶች ትዳርን የመከራና የስቃይ ቦታ ነው ብለውታል። በትዳር ውስጥ የባልና የሚስት ስነፆታዊ ሚና እየተቀየረ ነው። መፋቀር፣መተማመንና መከባበር የተባሉ የትዳር እሴቶች በትዳር ውስጥ እየፈረሱ ነው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል። ከውጤቶች በመነሳትም የቤተሰብ ብሎም የሀገር ግንባት መሠረት የሆነው ትዳር መዋቅሩ እየተናጋ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። ከድምዳሜው በመነሳትም ተመራማሪዎች በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊና ተከታታይ ጥናቶችን ቢያደርጉና የይሁንታ ሀሳብ ቢሰጡ፣ ጥሩ ሀገር የጥሩ ቤተሰብ ውጤት ነውና የማህበረሰብ ህልውና ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ጥሩ ቤተሰብ መገንባት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ቢረባረቡ ዛሬ እየደረሰ ያለውን ምስቅልቅልና ነገ ሊደርስ የሚችለውን የሀገር መፍረስ አደጋ ለመከላከል ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል የሚል የይሁንታ ሀሳብ ተሰጥቷል።*

**ቁልፍ ቃላት** ፡- *ቀልድ፣ትዳር፣ የስነፆታ ሚና፣ የትዳር እሴቶች*

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ዋና ከሆኑ አያሌ ጉዳዮች አንዱ በሆነው በትዳር ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ትዳር አብዛኛው የዓለማችን ማሕበረሰብ የሚከውነው ተግባር ነው። በተለያየ ባህል ውስጥ የሚፈፀም እንደመሆኑም ወጥ ብያኔ የለውም። ለትዳር

ከተሰጡ ብያኔዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት (1993፣217) ትዳርን ‹‹ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው እንዲኖሩ የሚያስችላቸው፣ በቃል ኪዳን የታሰረና ህጋዊ የሆነ ጥምረት፣ አንድነት፤ የባልና ሚስት የአንድነት ኑሮ፤ ትዳር፣ ቤት፣ ንብረት፤ ባል ወይም ሚስት›› ሲል በይኖታል፡፡ ደስታ ተክለወልድ (1962፣216 ) ትዳርን፣ "መዛመድ፣ ባልና ሚስት መኳኋን፣ ማቀናጀት፣ ማራከብ፡ ማገናኘት፣ ማዛወግ" በማለት ይፈቱታል ፡፡ በእነዚህ ብያኔዎች ትዳር ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ግለሰቦች ለመዛመድ ሲሉ የሚፈጥሩት ውህደት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የመገናኘቱ ዓላማ ዝምድናን ፍለጋ የሚል ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ (Stewart, 2006) "ትዳር አንድ ወንድና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው ለመኖርና ህጋዊ፣ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ሃላፊነትን ለመውሰድ ተስማምተው በተለያየ የስርዓት አይነት፣ ቤተሰባዊ ትስስር ለመፍጠር፣ የሚመሰረት በህግ እውቅና የተሰጠውና የጋራ ጥቅም፣ ኃላፊነትና ግዴታ የሚያስከትል እንዲሁም የዝምድና ትስስር የሚመሰረት ግንኙነት በማለት ሲተረጉሙት Sherif, Rayn and Robert (2012 ) ደግሞ "ትዳር ማለት በስነ ልቦና፣ በስነ አእምሮአዊ እና አካላዊ ጥምረት ቤተሰብ ለማስተዳደር ወይም ለመምራት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ባልና ሚስት ሆነው የሚጣመሩበትና ያዳበሩቸውን ማህበራዊ ዕሴቶች በህግ አግባብ የሚተገብሩበት ሂደት ነው/ Marriage is a comprehensive union of mind and body ordered to family life, unites a man and a woman as husband and wife, They document the social values of applying this principle in laws" በማለት በይነውታል፡፡

ከላይ የቀረቡ አራት ጥቅሶች ለትዳር የሰጧቸውን ትርጓሜዎች ጠቅለል አድርገን የጋራ ሀሳባቸውን ስንወስድ ትዳር የሁለት ሰዎች (ሴትና ወንድ) ሁለንተናዊ ትስስር አንድ መሆን፤ ዝቅ ሲል ለቤተሰብ ከፍ ሲል ደግሞ ለማህበረሰብ ምስረታ መሰረት መጣል አድርገን ልንረዳው እንችላለን፡፡ ይሁንና በአሁኑ ዘመን የትዳር ትርጉም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ እንደ የተጋቢዎች ጾታ፣ ትዳሩ የሚፈፀምበት ዓላማ፣ የተጋቢዎች የመመራረጫ መስፈርት አይነት የመሳሰሉ ጉዳዮች መኖራቸውን ፀሀፍት ይገልፃሉ Gary (2014)፡፡ ይህ ሁኔታም በተለያየ መንገድ ሲንፀባረቅ ይታያል፡፡ ፎክሎር የሰው ልጅ በእለት ከእለት ህይወቱ ውስጥ እያከናወናቸው ያሉ ድርጊቶች የሚገልፅበት አንድ መንገድ ነው፡፡ ትዳርም የሰው ልጅ አንድ የህይወት ገፅታ ነውና በተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች አማካኝነት ይገለፃል፡፡ ለምሳሌ የግለሰብ የህይወት ልምድ ተረኮች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ቃል ግጥሞች የትዳር መልክ የሚገለፅባቸው ፎክሎሮች ሲሆኑ ቀልዶችም እንዲሁ አሁን ላይ የትዳር መልክ ምን እንደሚመስል ከሚያሳዩ ጉዳዮች ውስጥ አንድ መንገድ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት የትዳርን ጉዳይ ለመመርመር ከስነቃል ዘርፎች ውስጥ ቀልድን ተጠቅሟል፡፡

ቀልዶች በፎክሎር የጥናት መስክ ውስጥ በቋንቋ አማካኝነት የሚተላለፈውና ስነቃል ተብሎ የሚጠራው ፎክሎር ንዑሳን ዘርፎች ናቸው፡፡ ስነቃል ደግሞ የሰው ልጅ ሀዘኑንና ደስታውን፣ እምነቱንና አስተሳሰቡን፣ ድጋፉንና ተቃውሞውን በአጠቃላይ ሰዋዊ ስሜቱን ለመግለፅ ሲጠቀምባቸው ከኖሩ መንገዶች ውስጥ አንዱ ነው

(ዘሪሁን፣1991)፡፡ ቀልዶች ይህንኑ የስቃልን ተግባር ይጋራሉ፡፡ ይሁንና እንደአንድ የስነቃል ዘርፍ የራሳቸው መልክም አላቸው፡፡ ይኸውም ፈገግ እያሰኙ ቁምነገርን ማስተላለፍ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ Ahuja and bali (2018) ‹‹Humor is the tendency of specific cognitive actions to cause laughing and amusement./ ቀልድ እያሳቀና እያዝናና ቁም ነገር የማስጨበጥ ባህርይ ያለው ተግባር ነው››፡፡ ሲሉ Attardo, (1994) **ደግሞ** "Humor is a universal phenomenon, but the linguistic realization of humor varies across languages and cultures, reflecting different social norms, values, and linguistic resources/

ቀልድ ከቋንቋ አጠቃቀሙ ከቋንቋ ቋንቋ፤ከባህል ባህል ቢለያይም በሁሉም ቋንቋ ንግግሮች ውስጥ የሚገኝ የተለያዩ ደንቦችን እሴቶችንና የቋንቋ ሀብቶችን የሚያንፀባርቅ ክስተት ነው›› ብለዋል፡፡

ይህ ጥናት ትኩረቱን ትዳርን አስመልክቶ በሚቀለዱ ቀልዶች ላይ አድርጓል፡፡ ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አነሳሽ ምክንያት በኢመደበኛ እይታም ቢሆን ሰዎች ሰርግን በሚያዩበበት ጊዜ የሚሰጡት ‹‹አሁን ለሚፋቱት፣ ይህንን ያህል ልፋት›› የሚሉ ተደጋጋሚ የተስፋ መቁረጥ አስተያየቶችን መስማት፣ ሁለተኛው በመኖር ሒደት እየታዩ ያሉ በቀላሉ የመጋባትና በቀላሉ የመፋታት ምልከታዎች፣ ሶስተኛው በእነዚህ ምልከታዎች መነሻነት በተደረገ አሰሳ በአሁን ጊዜ ምን ያህል ትዳሮች እየተፈፀሙ ነው? በየጊዜው ከሚፈፀሙ ትዳሮችስ ምን ያህሉ ዘላቂ ናቸው? ለሚለው ጥያቄ የተገኙ መልሶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ https://am.al-ain.com/article/basic-concerns-before-you-get-marry የተባለ ድረ ገፅ በዓለማችን በየዕለቱ 115 ሺህ ትዳሮች የሚመሰረቱ ሲሆን ከቅርብ ዓመት ወዲህ ደግሞ የተጋቢዎች ቁጥር እየቀነሰ ሲመጣ የፈረንጆቹ 2021 ደግሞ በ50 ዓመት ታሪክ ዝቅተኛ ትዳር የተመሰረተበት ዓመት ሆኖ ተመዝግቧል ያለ ሲሆን፤ የአሜሪካ ድምፅ ሬዴዮ ከኢትዮጵያ ሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ ባለሙያዎች ጋር ባደረገው ቃለመጠይቅ ከመስሪያ ቤቱ ባለሙያዎች በተገኘ መረጃ ‹‹በአዲስ አበባ ከተማ ፍቺ ፈፃሚዎች እየጨመሩ ነው››፡፡ ባለሙያዎቹ እንዳሉት በ2015 ዓ.ም 4996 ፍቺዎች የተመዘገቡ ሲሆን ይህ በ2014 ከተፈፀመው እጥፍ ነው፡፡ ይህ ቁጥርም የተመዘገበውን የፍቺ ቁጥር ይመለከታል እንጅ በየአካባቢው የተፈፀመው ፍቺ ከዚህ በላይ እንደሚሆን ይገመታል ብለዋል፡፡ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ዛሬ ዛሬ ሰዎች ስለትዳር የሚሰጧቸው አስተያየቶች የትዳር ሁኔታ ችግር ውስጥ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሲቪል ምዝገባና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ መረጃም ይህንኑ ሀሳብ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ መረጃ ትዳር በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ካለው ዋጋ አንፃር የመፍትሄ ሀሳብ መስጠት ተገቢ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ስለዚህም በውጫዊ አተያይ ከተገኙ መረጃዎች ባሻገር በውስጣዊ (በራሱ በማህበረሰቡ) በሚገኙ መረጃዎች ሀሳቡን የመመርመር ፍላጎት ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደጥናቱ አድራጊ እምነት በቀልዶች ላይ የሚሰሩ ምርምሮች ሊያስገኙ ከሚችሉት ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊ፣ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አንፃር በቀልዶች ላይ ብዙ ምርምሮች ሊሰሩ የሚገባ ቢሆንም በርዕሰ ጉዳዩ ብዙ ምርምሮች የሚስፈልጉ ቢሆንም የተደረገው የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

እስከሚያሳየው ድረስ ‹‹ቀልድን›› ርዕሰ ጉዳይ አድርገው የተሰሩ ጥናቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

ሰርካለም በሪሁን (2011 ዓ.ም) "ወቅታዊ" (ከመጋቢት 2010 መጋቢት 2011) የፌስቡክ ፖለቲካዊ ቀልዶች አውዳዊ ይዘትና እንድምታ››፣ በመልሰው በሪሁን (2012 ዓ.ም). ‹‹ ጥርጣሬ፡- በፌስቡክ ቀልዶች ውስጥ ››, በViriya (2015) ‹‹Styles and types of humor and virality of memes of facebook››: የሚሉ የፖለቲካንና የስነልቡናን ጉዳይ በቀልድ ውስጥ ያዩ ጥናቶች ሲኖሩ፣ ከትዳር አንፃር በዝናሽ ሰለሞን (2004 ዓ.ም)፣‹‹የሀድያ ብሄረሰብ የባህላዊ ትዳርና የሰርግ ስነ ስርዓት›› በአፈወርቅ ተፈራ (2009 ዓ.ም) ‹‹የሰርግ ስነ ስርዓት ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ በሃራና አካባቢው ማህበረሰብ››፤ በገነት ስመኝ (2012)፣‹‹በባህላዊ የትዳር ሥርዓት ውስጥ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች አንድምታና ፋይዳ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ›› የሚሉ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ትዳር ላይ የተሰሩ ጥናቶች ዋና ትኩረታቸው ባህላዊውን የትዳር ስርዓት ክዋኔውንና ለማህበረሰብ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑ የቀደምት ጥናት አሰሳ ውጤቱ ትዳርንና ቀልድን ለየብቻ የመረመሩ እንጅ ይህ ጥናት ሊሰራበት ከታቀደው አቅጣጫ አንፃር ትዳርን በቀልዶች ይዘት አማካኝነት የመረመሩ አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታም ለጥናቱ መሰራት ሌላው ገፊ ምክንያት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትዳርን አስመልክቶ የሚነገሩ ቀልዶችን ይዘት መመርመር ነው፡፡ ይህ ዋና ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ጥናቱ በቀልዶች አማካኝነት ትዳር እንዴት ተገልፆአል? ቀልዶች በትዳር ውስጥ የስነፆታን ሚና እንዴት ገልፀውታል? ቀልዶች የትዳር እሴቶችን እንዴት አቅርበዋቸዋል? የሚሉ ጥያቄዎች አዘጋጅቶ መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህ ጥናት መደረጉ በርካታ ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለማህበራዊ እሴቶች መላላት ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የትዳርን ሚና ለአንባቢ ይጠቁማል፡፡ የትዳርን ወቅታዊ መልክ እና እየሄደበት ያለውን መጪ ጊዜ ለአንባቢ ይጠቁማል፡፡ በቤተሰብና በማሕበረሰብ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብ ይሆናል፡፡ በቤተሰብና ማሕበረሰብ ዙሪያ ለሚሰሩ ተቋማት የትኩረት አቅጣጫዎችን ያመላክታል፡፡

ጥናቱ ከይዘት፣ ከጊዜ፣ከቦታና ከቋንቋ አንፃር የተወሰነ ነው፡፡ የትዳር ጉዳይ በሌሎች የስነቃል ዘርፎች የሚነገር ቢሆንም ቀልዶች ካላቸው እያሳቁ ቁምነገርን የማስጨበጥ እንዲሁም ወግቶ ያለማሳመም ባህርይ ጥብቅ ቁምነገር የሆነውን ትዳርን ለመመርመር አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ተመርጠዋል፡፡ ትዳር ተፈጥሯዊ ተግባር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የረጅም ዘመን እድሜ ባለቤት ነው (ዘፍ 1፤28)፡፡ ቀልዶችም እንዲሁ ከሰው ልጅ ዕድሜ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዕድሜ እንዳላቸው ይገመታል (Bergson ፤2003)፡፡ ይሁንና ጥናቱ ወቅታዊውን የትዳር ሁኔታ ለመመርመር ያለመ በመሆኑ አሁን ላይ በመነገር ላይ ያሉትን ቀልዶች በመረጃነት ተጠቅሟል፡፡ ጥናቱ ለጥናቱ አድራጊ ካለው ምቹነት አንፃር ባህርዳር ከተማን ወቅታዊ መረጃ የሚገኝበት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የመረጃ መረብን የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታ በማድረግ ተወስኗል፡፡

ቀልዶች በሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ የሚነገሩ ቢሆንም ይህ ጥናት የተወሰነው በአማርኛ ቋንቋ ብቻ በቀረቡት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በእነዚህ ሁኔታዎች እንዲገደብ የአጥኝዋ የጊዜ፣ የገንዘብ፣የቋንቋ አቅም ምክንያቶች ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ሰዎች ለትዳር ያላቸውን እሳቤ፣ እምነትና ርዕዮተዓለም የሚያጠና እንጅ ከአሀዛዊ ጉዳዮች ጋር የማይነካካ በመሆኑ ምርምሩ አይነታዊ ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ቀዳማይ ምንጮች ሁለት አይነት ናቸው፡፡ እነሱም ቀልድ እንደሚውቁ በአካባቢው ሰዎች የተመሰከረላቸው ሰዎች፤ ባለትዳሮች እና የተለያዩ የመረጃ መረቦች ናቸው፡፡ መረጃዎች በቃለመጠይቅ እንዲሁም በንባብ ተሰብስበዋል፡፡ በቃለመጠይቁ ከሰባት ዓመት በላይ በትዳር የቆዩ አስር ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ስለ ትዳር ያላቸውን እሳቤ በመግለፅ እንዲሁም ትዳር ላይ የተቀለዱ ቀልዶችን በመንገር ተሳትፈዋል፡፡ ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች እንዲሁም መረጃ ሰጪዎች ስለጉዳዩ እውቀት ያላቸው በሚል ፍረጃ በዓላማ ተኮርና በአመቺ የንሞና ዘዴ የተገኙ ናቸው፡፡

የተሰበሰቡት መረጃዎች በጥናቱ አላማ የተነሱ ጥያቄዎችን ከመመለስ አንፃር በይዘታቸው ተመድበው በመዋቅራዊ (britannica.com,2025) እና በ‹‹ሒውመር›› (Perkins, 2023) ንድፈ ሀሳቦች ተተንትነዋል፡፡ መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ የተለያዩ አተያዮች ያሉት ሲሆን ይህ ጥናት ባህልን በአቻ ተቃርኖዎች እና በሰዎች እውቀት ጥልቅ መዋቅር (አወቃቀር) የመረዳት ዘዴ ነው፡፡ የሚለውን የሌቪ ስትራውስን አተያይ መሠረት አድርጎ መረጃዎችን ተንትኗል፡፡ በዚህ ጥናትም በትዳር ቀልዶች ውስጥ፣ በወንድና በሴት ሚናዎች መካከል ያለውን ስሜት፣ ወይም ትዳር ሊሆን ይገባል በሚባለው ዕውቀትና በእውነተኛው ህይወት ውስጥ ባሉ ልዩነቶች መካከል ትኩረት ተደርጎ ንድፈ ሀሳቡ መረጃ ተተንትኖበታል፡፡

ሒውመር ንድፈ ሀሳብም እንዲሁ የተለያዩ አተያዮች አሉት፡፡ ጥናቱ የቶማስ ሆብስን Superiority Theory/የበላይነት (17ኛው ክፍለ ዘመን) እና የኢማኑኤል ካንትን (18ኛው ክፍለ ዘመን) Incongruity Theory/ ያለመመጣጠን ንድፈ ሀሳቦች ተጠቅሟል፡፡ Superiority Theory (የበላይነት ንድፈ ሀሳብ) ይህ ንድፈ ሃሳብ ቀልድ የሚነሳው ከሌሎች እንደምንበልጥ ሲሰማን ነው ይላል፡፡ በትዳር ቀልዶች ውስጥ፣ የቀልዱ አሳቂነት የሚመጣው የአንድ አጋር (ብዙውን ጊዜ ባል) ካለው ብቃት ማነስ ወይም ከማይመስል ወይም ሁለቱም አጋሮች በአንድ ጉዳይ ውስጥ ከሚኖራቸው የተጋነነ የብቃት ማነስ ነው የሚል ሲሆን Incongruity Theory (አለመመጣጠን ንድፈ ሀሳብ) እንደሚያሳየው ደግሞ ቀልድ የሚመነጨው በሚጠበቀው እና በእውነታው መካከል አለመጣጣም ሲኖር ነው፡፡ የትዳር ቀልዶች ብዙውን ጊዜ በባልና ሚስት መካከል አለ በሚባለው ምናባዊ ፍቅር እና ዕለት ተዕለት በሚታየው ምስቅልቅል እውነታ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ተመስርተው ይፈጠራሉ፡፡ ለምሳሌ ለራስ ከተሰጠ ግምት የተነሳ  በቤት ውስጥ የሚኖር ሚናን ካለመቀበል የሚመጣ “የጾታ ጦርነት” ወይም ጥንዶች በውጪ ያላቸው ህዝባዊ ምስል እና በግል ሕይወታቸው መካከል ያለ አለመግባባት የማይመጣጠን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ነው ተብሎ

የሚታሰበውንና ያለውን እውነታ ማሳየት እንዲቻል ከሰዎችና ከመረጃ መረብ የተሰበሰቡ መረጃዎች መዋቅራዊና ሒውመር ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 2. የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል ከቀዳማይ ምንጮች የተገኙ ጥሬ መረጃዎች ከካልዓይ ምንጪ በተገኙ መረጃዎች እየተወዳደሩና እየተነፃፀሩ በዓላማነት የተነሱ ጥያቄዎችን ከመመለስ አንፃር ተመድበው ተተንትነዋል፡፡

### 2.1. ትዳር ምንድን ነው?

ከዚህ ቀጥሎ በውስጣቸው ትዳር ምንድን ነው? እንዴትስ ተገልጧል? የሚለውን ሀሳብ ያሳያሉ የተባሉ ቀልዶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ትንተናው ቀልዶች የያዙት ሀሳብ ለመረጃ መተንተኛ በተመረጠው የአለመመጣጠን ንድፈ ሀሳብ እሳቤ መሰረት ስለትዳር ያለው ነባር እሳቤ ምንድን ነው? ይህ እሳቤ ቀልዶች ውስጥ እንዴት ቀርቧል? በሚል ቅጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. *አንዱ ደሞዙ ሰባት ሺህ ብር ነው፡፡*

*ጓደኛው አንተ ትዳር የምትይዝ መቼ ነው ብሎ ጠየቀው፡፡*

*ይህንን የጥላቻ ንግግር ሁለተኛ እንዳትናገረኝ ብሎ መለሰለት፡፡ (ፌስ ቡክ)*

2. *ፍቅር ክፉ ‹‹ደዌ›› ነው፡፡ መድሐኒቱ ደግሞ ትዳር ነው፡፡ (ፌስ ቡክ)*
3. *ልጅ፡- ወደእናቱ ይመጣና፤ ‹‹እናቴ ጉድ ሆንኩኝ፤አግባ አግባ ብለሽኝ ይኸው እንዴት እንደከሳሁ ሱሪዬ ከላዬ ላይ ሊወልቅ ነው›› ይላል*

*እናት፤- አይ ልጄ ገና ምኑን አይተከው፤ስጋህ ከላይህ ላይ ያልቅና፤ አጥንትህ ይወልቅና*

*ሰው ነው ከመንገድ አንስቶ የሚሰጥህ፤*

Rayn and Robert (2012), Stewart, (2006) እንደሚሉት ትዳር በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ለባልነትና ለሚስትነት የሚደረግ ህጋዊ ጥምረት ነው፡፡ ትዳር ባልና ሚስት ሆነው ለመኖር የተስማሙ ሰዎች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሮአዊና መንፈሳዊ አንድነት ፈጥረው የሚኖሩበት መንገድ ነው፡፡ ይህ መንገድ ከሁለቱ ተጋቢዎች አልፎ በሁለቱ መካከል የሚገኙ ሰዎችን በዝምድና የሚያስተሳስር፣ በባልና ሚስቱ እንዲሁም በማህበረሰቡ መካከል ትስስር የሚፈጥር ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ህጋዊ ሃላፊነት እና ግዴታን የሚያስከትል ግንኙነት ነው፡፡ ይህንን ንድፈ ሀሳባዊ ትርጓሜ በመያዝ ትዳር ላይ የተቀለዱ ቀልዶችን ይዘት ስንመለከተው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በተራ ቁጥር አንድ የቀረበውን ቀልድ ስንመለከት ትዳር አስቸጋሪ ህይወት የሚመራበት ተቋም እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በነባሩ ማህበራዊ የአኗኗር ልምድ አንድን ሰው ‹‹አግባ›› ወይም ‹‹አግቢ›› ብሎ መምከር ከበጎ አሳቢ ጓደኛና ከተቆርቋሪ ቤተሰብ የሚሰጥ ምክር ነበር፡፡ በዚህ ቀልድ ግን አግባ ብሎ መምከርን ለሚጠሉት ሰው የሚያደርጉት ‹‹ስድብ›› በአጠቃላይም ‹‹የጥላቻ ንግግር›› ሆኖ ቀርቧል፡፡ የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚሉት ‹‹የጥላቻ ንግግር›› ከትንሹ ንዴትን ብስጭትን ለማውጣት ከሚደረግ ጀምሮ ሰዎችን ‹‹አያስፈልጉም፣ ይወገዱ›› እስከሚለው የሚደርስ ንግግር ነው፡፡ ይህ ንግግር በሀብታቸው፣ ወይም በጎሳቸው፣

በቋንቋቸው ወይም በእምነታቸው ምክንያት በሌላው ዘንድ የተጠሉ ሰዎች የሚፈረጁበት፤ ከፍረጃም በላይ ሰብእናቸው የሚገፈፍበት ንግግር ነው›› (ዘነበ በየነ፣የራስ ወርቅ አድማሴ፤2008)፡፡ በዚህ ቀልድ ‹‹አግባ›› የሚለው ምክር ይህንን አይነት ትርጉም ካለው ንግግር ጋር አቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በቀልዱ ‹‹አግባ›› ተብሎ የተመከረው ሰው ደምወዙ ሰባት ሺህ ብር ነው፡፡ ተመካሪው በሰባት ሺ ብር ደምወዝ ‹‹አግባ›› ተብሎ መመከሩን ስድብ፤ከስድብም የጥላቻ ንግግር ሲል ፈርጆታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተገኙ የቃል መረጃዎች ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይህንኑ የሚደግፍ ነው፡፡

> *ሰባት ሺህ ብር ትዳር ለመመስረት በጣም ከባድ ነው፡፡ ዛሬ ከአምስት ሺህ ብር በታች ቤት ኪራይ አይገኝም፤ መጀመሪያ ሰው በፍቅር ተነሳስቶ ቢጋባም እንኳን ችግሩ ፍቅሩን ያናጋዋል፡፡ ኑሮ ተወዷል፡፡ በዋናነት ቤት ኪራይና ምግብ ትልቅ ወጪ ናቸው፡፡ እና ሰባት ሺ ብር ምናልባት ለነባር ትዳር እንደሁ እንጅ አዲስ ለሚጀመር ትዳር በቂ አይደለም፡፡ (ዋሲሁን ለገሰ፣ቃለመጠይቅ፤19/06/2017 ዓ.ም)*

መረጃው ከላይ በቀልዱ የቀረበውን ሀሳብ ይደግፋል፡፡ በቀልዱ ውስጥ ‹‹ሰባት ሺ ብር ትዳር ለመያዝ በቂ አይደለም›› የሚል መልዕክት ይተላለፋል፡፡ ከላይ የቀረበው የቃለመጠይቅ መረጃ እንደሚገልፁት ሰባት ሺህ ብር ትዳርን ለመመስረት በቂ ገንዘብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ትዳር መያዝን ተከትሎ የተለያዩ ወጪዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በዚህ የገንዘብ አቅም ሊሸፈኑ አይችሉም፡፡ ተመካሪው ትዳርን የፈራበት ምክንያቱም ይኸው የኢኮኖሚያ አቅሙ ይመስላል፡፡ በመሆኑም የሰባት መቶ ብር ደምወዝ ያለውን ሰው ትዳር ያዝ ብሎ መምከር ሰውዬው ወደችግር እንዲገባ ማበረታታት ይመስላል፡፡ ይህም በመሆኑ ተመካሪው ምክሩን ‹‹የጥላቻ ንግግር›› ሲል ጠርቶታል፡፡ በቀልዱ ትዳር ይዟቸው ከሚመጣቸው የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አንፃር ባገባ ‹‹ይደርስብኛል›› ብሎ ካሰበው የኑሮ ጫና በመነሳት አግባ የሚል ምክር ከጥላቻ ንግግር ተፈርጆ ይታያል፡፡

ወደ ሁለተኛውና ሶስተኛው ቀልድ ስንሄድም የምንመለከተው ሀሳብ ከዚሁ፤ ትዳር ምን ያህል ከባድ ጉዳይ መሆኑን ከሚነግሩ ይዘቶች ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ በተራ ቁጥር ሁለት የቀረበው ቀልድ ሰዎች ትዳር ከያዙ በኋላ በጓደኝነት ዘመን በመካከላቸው የነበረው ፍቅር የሚጠፋ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ይህ ቀልድ፣ሰዎች ከፍቅረኝነት ወደ ባልና ሚስትነት ሲመጡ የሚፈጠረውን የስሜት ለውጥ የሀሳቡ ማጠንጠኛ አድርጎ አንስቶታል፡፡ እርግጥ ነው ሰዎች ወደትዳር ሲገቡ በፍቅረኝነት ወቅት ያልነበሩ ሀላፊነቶችን ይሸከማሉ፡፡ ይህ በመሆኑም ጊዜያቸውንና ስሜታቸውን ለተሸከሟቸው ኃላፊነቶች የሚከፋፍሉ በመሆኑ የፍቅር ስሜትን በመገላለፅ በኩል በፍቅረኝነት ዘመን በነበረው ሁኔታ ላይቀጥሉ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታም በቀልዱ ውስጥ ትዳርን የፍቅር ማርከሻ ሆኖ እንዲቀርብ አድርጎታል፡፡

ሶስተኛው ቀልድ ደግሞ እናት የትዳርን አስጨናቂነት ለልጃቸው ሲያስረዱ የምናይበት ነው፡፡ በቀልዱ ልጅ እናቱ ስለመከሩት እንዳገባ ይገለፃል፡፡ ይሁን እንጅ እናት ምንም እንኳን ልጃቸውን እንዲያገባ

በተደጋጋሚ ጠይቀውት ያገባ ቢሆን፤በትዳር ውስጥ ሊያጋጥመው የሚችለውን ስቃይ አስቀድመው ያውቃሉ፡፡ ትዳር እንደሚከሳ እንደሚያጠቁር፤ ስጋን ጨርሶ በአጥንት እንደሚያስኬድ ይነግሩታል፡፡ ይህም በትዳር ምክንያት በሰዎች ላይ ከሚጫነው ሀላፊነት የሚመጣ ነው፡፡

ቀጥሎ የቀረበው ቀልድም ከላይ ከቀረቡ ሀሳቦች ጋር ተመሳሳይ ይዘት እንዳለው ይታያል፡፡

4. *የድሮ ጓደኞች ይገናኙና ስለአለፈው ጊዜና ስለድሮ ጓደኞቻቸው ይጠያየቃሉ፡፡ አንደኛው ሌላውን የድሮ ጓደኛቸውን ስም ጠርቶ ‹‹እንትናስ እንዴት ነው? ›› ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ጓደኛውም ‹‹እሱ እኮ አገባ›› ይለዋል፡፡ አገባ?!፣ የታባቱ ይበለው! በጣም ክፉ ነበር! አለው፡፡ (እመቤት ሙሉ፣ ቃለመጠይቅ፣01/04/2017፣ባሕር ዳር)*

ነባር ባህልና ልምዱ እንዲሁም አስተሳሰቡ ማግባት መውለድ የጤነኛ ማህበረሰብና ግለሰብ ተግባር ነው ይላል፡፡ ሰዎችም በሀይማኖታዊ ብሎም በማህበራዊ አስተሳሰብ ትዳር ለመረዳዳት፣ ዘር ለመተካት፣ እና ሰዎችን ከዝሙት ጠንቅ ለመጠበቅ ለሚሉ ሶስት ዓላማዎች ተመስርቷል ሲሉ እንደሚያምኑ ከቃለመጠይቆች (ወ/ሮ የሺእመቤት አዲስ፤ 07/04/2017፣ ቃለመጠይቅ) አባ ገብረ ማርያም ስንሻው 09/05/2017፣ ቃለመጠይቅ) እንዲሁም ከንባብ (https://www. dmeyesus. org/wedding) የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይሁንና ቀልዱ ማግባትን እንደችግር አለማግባትን ደግሞ እንደጥሩ እድል ሲቆጥር ይታያል፡፡ በመሆኑም በጓደኛሞች መካከል ‹‹ክፉ›› ተብሎ የሚታሰበው ግለሰብ ጥሩ የቅጣት ቦታ ውስጥ እንዳለ ተስሎ ይታያል፡፡ ምክንያም ቀልዱ ትዳርን ክፉና አስቸጋሪ ለሆኑ ሰዎች የቅጣት ቦታ አድርጎ አቅርቦታል፡፡

5. *ከእለታት አንድ ቀን ታክሲ እየጠበኩ ቆሜያለሁ ፣ ሁለት እናቶች ከፊቴ ነበሩ ፤ የሆነች ልጅ በዛ እያለፈች ተያዩና ደመቅ አድርገው ሰላም ካሏት በኋላ አንደኛዋ እናት "ትዳር ተስማምቶሽ የለም እንዴ ብርቱካን መሰልሽኮ" አሉ አ.ጋነው! ልጅቱ "ኧረ አላገባሁም" አለች በትህትና እየሳቀች፡፡ ተሰነባብተው ልጅቷ አለፍ እንዳለች "ታዲያ ምን ሆና ነው እንደዚህ የጠቋቆረችው?" ብላ እርፍ፡፡ (ፌስ ቡክ፤ኮተቤ ፕረስ)*

ይህ ቀልድ የሁለት እናቶችን ሀሜት ያሳያል፡፡ ሰዎች ከስታና ጠቁራ ያዩአትን ሴት የመጎሳቀል ምክንያት ከትዳር በስተቀር ሌላ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አላደረባቸውም፡፡ ስለዚህም ይህንን ለማውጣጣት ሲሉ ከሆነችው በተቃራኒ ‹‹ትዳር ተስማምቶሻል›› ሲሉ ወሬያቸውን ይጀምራሉ፡፡ አለማግባቷን ስትነግራቸው ግን የችግሯ ምንጭ ትዳር ነው ብለው በመደምደማቸው መክሳት መጥቆሯ ጥያቄ ይሆንባቸዋል፡፡ ትዳር ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ብዙ ሀላፊነቶችን ይዞ እንደሚመጣ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ያገባ ሰው የተለያዩ ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ሀላፊነቶችን መሸከሙ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሀላፊነት ግን ለሁሉም ሰው ከባድ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንስ

የትዳር አንዱ አላማው መረዳዳት እንደመሆኑ በመረዳዳትና በፍቅር ኑሮን አቅልለው የሚኖሩ ብዙዎች አሉ፡፡ በማግባታቸው ምክንያት ህይወታቸውን በራሳቸው ሀላፊነትና መንገድ ስለሚመሩ ተደስተውና ኑሮ ተመችቷቸው የሚኖሩ በርካታ ሴቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው የቃል መረጃ ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ ነው፡፡

> *ኸረ የእኔን ኑሮ ብታይው እኮ . . . እኔ ለሴቱ ሁሉ የእኔን ይስጠው እላለሁ፡፡ በጣም ተከባብረንና ተዋድደን ነው የምንኖረው፣ እንደልጅ እኔን ሲንከባከብ ነው የሚውለው፤ከፍቶኝ ማየት አይወድም፤እኔም እንደእሱ ነኝ፡፡ ይህንን ስልሽ ግን ሁልጊዜ ሰላም ነው ማለቴ አይደለም፤ የምንጣላበት፣ ሁኔታዎች የሚከብዱሽ ቀንም አለ፡፡ ግን እነዚህ ቀናት ከመልካሙ ቀን አይበልጡም፡፡ ብቻ ምናለፋሽ ትዳር ለሴት ልጅ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ (በሰና እንየው፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/04/2017፣ ባሕር ዳር)፡፡*

የቃል መረጃው ለአንድ ሰው በተለይም ለሴት ልጅ ትዳር በጣም አስፈላጊ ነገር መሆኑን ይገልፃል፡፡ መረጃ ሰጪዋ የራስዋን ህይወት ዋቢ አድርገው እንደገለፁት ምንም እንኳን ፍፁም ነው ባይባልም ትዳር መረዳዳትና መተጋገዝ ያለበት ተቋም በመሆኑ የተነሳ ለሰዎች ምቹ ቦታ ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሁኔታም ከሞላ ጎደል በአብዛኛው ሰው ህይወት ውስጥ የሚንፀባረቅ ነው፡፡ ይሁንና በቀልዱ የቀረበው ሀሳብ ትዳር ያከሳል ያጠቁራል የሚል መልዕክት ያዘለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

> *6. ባል ከሥራ ይመጣና ሻወር ቤት ይገባል ፤በባልየው ስልክ ተደጋግሞ ይደወላል:: ሚስትም ስለተደጋገመ ስልኩን ሰታየው ‹‹ሀኒ›› ይላል ሚስት በጣም ትናደድና እኔን ማን ብሎ ነው የፃፈኝ ብላ በራሷ ስልክ ወደ ባልየው ስትደውል ‹‹ጓንታናሞ›› የሚል ስም ወጣ፡፡ (አብነት ካሳ፣ 09/04/2017፣ ባሕር ዳር)*

በዚህ ቀልድ ትዳሩን የማያከብር ከህጋዊ ሚስቱ በላይ ሌላ ሴት በፍቅረኛነት የያዘ ሰው ታሪክ ቀርቧል፡፡ ሰውዬው ፍቅረኛውን ‹‹ሀኒ››/ ‹‹ማሬ›› ብሎ አቆላምጦ ይጠራታል፡፡ ባንፃሩ ስለትዳር ህይወቱ እጅግ ጥሩ ያልሆነ ስሜት እንደሚሰማው ማየት ይቻላል፡፡ ባል ትዳሩንና ሚስቱን ከፍተኛ የእስረኞች ስቃይ ይፈፀምበታል ተብሎ ከሚነገርለት ኩባ ከሚገኘው ጓንታናሞ ቤይ የተባለ እስር ቤት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ፍቅረኛውንና ሚስቱን የሚጠራባቸውን ቃላት ንፅፅር ስንመለከት ለትዳር ያለው ስሜት ምን ያህል የከፋ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

7.ሚስት፡- ውዴ የሰርግ ሰርተፍኬታችንን እያገላበጥክ ማየት ከጀመርክ አንድ ሰዓት ሊሆንክ ነው፤ምን እየፈለክ ነው?

ባል፡- ኤክስፓየርድ ዴቱ መች እንደሆነ ማወቅ ፈልጌ ነው፡፡ (በረከት ሐይሌ፣09/05/2017፣ ባሕር ዳር)

በዚህ ቀልድ ውስጥ ትዳሩን ለመፍታት ቀን የሚጠብቅን አባወራ ምስል እናያለን፤ (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ህግ 1995፡6) ‹‹ትዳር ለአካለ

መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዘለቄታው አብሮ ለመኖር በመወሰን በራሳቸው ምርጫ በህግ ለመዋሀድ ፈቅደው በይፋ የሚመሰርቱት ግንኙት ወይም በዚሁ ግንኙነት አማካይነት የሚመሰረት ህጋዊ ተቋም ነው ሲል እንደሚገልፀው ትዳር ዘላለማዊ ጥምረት ነው፡፡ በባህላዊው የትዳር ስርዓት ከሚፈፀሙ ውሎች ውስጥም ባልና ሚስት ከሞት በስተቀር በምንም ሁኔታ ውስጥ ላይለያዩ የሚገቡት ውል ዋናው ነው፡፡ ከላይ በቀረበው ቀልድ ውስጥ የምናያቸው ባልና ሚስትም ለዚህ ቃልኪዳን መገዛት ያለባቸው መሆኑ ይጠበቃል፡፡ ይሁንና በዚህ ቀልድ ውስጥ ባል ህይወቱን በሙሉ አንዴ ከተጣመራት ሚስቱ ጋር መዝለቅ አለመፈለጉንና ትዳሩ ሊያበቃ የሚገባበት ጊዜ እንዳለ መጠበቁን እናያለን፡፡ በመሆኑም በዚህ ቀልድ ውስጥ ከነባሩ ማህበረ ባህላዊ ስርዓት ያፈነገጠ እሳቤ ሲተላለፍ ይታያል፡፡

ከዚህ በላይ በቀልዶች አማካኝነት ለትዳር የተሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመፈተሽ ያስቻሉ ሰባት ቀልዶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ቀልዶች ለትዳር አዎንታዊ አመለካከት የላቸውም፡፡ የመጀመሪያው ቀልድ ትዳር በትንሽ ደምወዝ እንደማይመሰረት ሲገልፅ ሁለተኛው፤ትዳር ፍቅርን እንደሚያጠፋ፤ሶስተኛው ቀልድ፣ ትዳር የጉስቁልና ቦታ ነው ሲል ፤አራተኛው ቀልድ ትዳር የክፉ ሰዎች መቀጫ መሆኑን ያሳያል፣አምስተኛና ስድስተኛ ቀልዶች ትዳር ለሴቷ አጎሳቋይ ለወንዱ ደግሞ አሰቃቂ እስር ቤት ነው ሲሉ ሰባተኛው ቀልድ ደግሞ ትዳር የማብቂያ ጊዜ ሊኖረው እንደሚገባ የሚናገር ቀልድ ነው፡፡

በዚህ ጥናት መረጃዎች ሊተነተኑበት የተመረጠው Incongruity (አለመመጣጠን) የተሰኘ የቀልድ ንድፈ ሀሳብ እንደሚያሳየው ቀልድ የሚመነጨው በሚጠበቀው እና በእውነታው መካከል አለመጣጣም ሲኖር ነው፡፡ የቀደሙ ጥናቶች፣ ሀይማኖታዊ ስብከቶች ማህበራዊና ባህላዊ ልማዶች ትዳር ባልና ሚስት፣ በፈቃዳቸው የሚመሰርቱት፣ የመተጋገዝ፣ የመረዳዳትና ተግባር የሚከወንበት፣ የተከበረና ንፁህ ተቋም መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይሁንና ከላይ በታዩትና ሀሳባቸው በተተነተነው ቀልዶች ውስጥ የዚህ ሀሳብ ተቃራኒ ትርጉም ይገኛል፡፡ በእነዚህ በሰባቱም ቀልዶች ስለትዳር ያለው ነባር ትርጉም በተቃራኒ ሀሳብ ሲሞገት እናያለን፡፡ ይህ ሙግትም አለመመጣጠን ንድፈ ሀሳብ እንደሚለው ፈገግታን ይፈጥራል፡፡ ከላይ የቀረቡ ቀልዶችም ፈገግ የሚያሰኙ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ይሁንና Ahuja and Bali (2018) እንደሚሉት ‹‹ቀልድ ፈገግ እያሰኘ ቁም ነገር የሚያስጨብጥ ጥበባዊ ንግግር ነውና ከፈገግታው ባሻገር ከቀልዱ የሚገኘው ቁምነገር ምንድን ነው ስንል ነባሩን የትዳር ትርጉም ንዶ፣ ትዳርን የስቃይ፣ የእንግልትና የቅጣት ቦታ አድርጎ ማቅረብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ቀጥሎ በቀረበው ንዑስ ርእስ ደግሞ የትዳር እሴቶች በቀልዶች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ ታይቷል፡፡

## 2.2. የትዳር እሴቶች እንዴ ቀርበዋል?

ትዳር የተከበረ ማህበራዊ ተቋም እንደመሆኑ እንደየሚከወንበት ማህበረሰብ ዋጋ የተሰጣቸው እሴቶች አሉት፡፡ ያም ሆኖ መፋቀር መከባበር፣ እና መረዳዳት የብዙ ትዳሮች እሴቶች ናቸው፡፡ በብዙ ለትዳር ጥሩ ምሳሌ ተደርገው በሚነሱ ትዳሮች ውስጥ በባልና ሚስት መካከል ያለው ፍቅር፣ መከባበርና መረዳዳት አብይ ጉዳዮች ሆነው ይጠቀሳሉ (ጠና፤2008)፡፡ ከሀይማኖት አንፃርም ያየን እንደሆነ እነዚህ

ሀሳቦች የትዳር እሴቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ‹‹ይትባረክ እንደ አብርሃም፣ዘለዓለም›› (ሀገረሰባዊ ዘፈን) እየተባለ ውዳሴ የሚቀርብለት የአብርሐምና የሳራ ትዳር በመከባበር፣ በመረዳዳትና በመፋቀር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ (ዘፍጥረት 12 - 24) ይህንን ሀሳብ ይዘን ትዳር ላይ የተቀለዱ ቀልዶች ስለትዳር እሴቶች ምን ይላሉ የሚለውን እንይ፡-

*1. ልጅ ከእናቱ ጋ እየተወያየ ነው፡-*

*ልጅ፡ "እማዬ አንቺ ሰው የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ነው ትያለሽ፡፡ አባቴ ደግሞ ከጦጣ ነው*

*ይላል፤ የትኛው ነው እውነቱ?" ይላታል፡፡*

*እናት፡- "ልጄ መልሱ ቀላል ነው፡፡ አባትህ ስለ እሱ ቤተሰብ ነገረህ፤ እኔ ደግሞ ስለ እኔ ቤተሰብ*

*ነገርኩህ" (ፌስ ቡክ፣ኮተቤ ፕረስ)*

በዚህ ቀልድ ውስጥ ልጅ ለአንድ ጥያቄ ከእናትና አባቱ ዘንድ ያገኘው የተለያየ መልስ ግራ አጋብቶታል፡፡ ይህንን ግራ መጋባት ለማስተካከል የጠየቀው ጥያቄ ይዞት የመጣው መልስ ግን በባልና ሚስቱ መካከል ያለው ግንኙነት መከባበር የሌለበት እንደሆነ የሚሳይ ነው፡፡ ይህ ቀልድ የሰውን ልጅ አፈጣጠር አስመልክቶ ካሉ አመለካከቶች ውስጥ የቻርለስ ዳርዊንን ‹‹ ሰው በአዝግሞታዊ ለውጥ የተገኘ ነው›› (Darwin, 2003) የሚለውን እና ‹‹ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው (ዘፍ.1፡26) የሚለውን የባህሪያውያን (የሐይማኖታውያንን) አመለካከት መሠረት በማድረግ የተቀለደ ነው፡፡ ይህ ቀልድ የተቀለደበት ማህበረ ባህላዊ ዳራ፤የክርስትናም ሆነ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነ ማህበረሰብ ያለበት ከባቢ ነው፡፡ ስለዚህም ‹‹ሰው ከጦጣ መጣ›› የሚለው አባባል ‹‹ሰው በፈጣሪ አምሳል ተፈጠረ›› ከሚለው ጋር በእጅጉ የራቀና ያነሰ ዋጋ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም እኔ አምላክ ፈጠረኝ አንተ ደግሞ ከጦጣ ተፈጠርክ የሚለው አባባል ራስን ከፍ ከማድረግና ሌላውን ዝቅ ከማድረግ ስሜት የሚመጣ ይሆናል፡፡ ቀልዱ በትዳር ውስጥ ያለውን የባልና ሚስት የግንኙነት አይነት ማሳያ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዚህ ቀልድ ውስጥ እናት ለልጇዋ በምትሰጠው ምላሽ የባሏን ቤተሰብ ‹‹ጦጣ›› ነው ትላለች፡፡ በዚህም ባሏን የማታከብረው መሆኑን፣ ባሏን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቹንም እንደማታከብር ማየት ይቻላል፡፡

*2. እሷ፡ ስንጋባ ጫት መቃምህን ታቆማለህ.*

*እሱ፡- እሺ*

*እሷ፡- ሲጋራም ማጨስ አትችልም*

*እሱ፡- እሺ*

*እሷ፡- የሰካራም ሚስት እንድባልም አልፈልግም ስለዚህ መጠጥም ማቆም አለብህ*

*እሱ፡- እሺ*

*እሷ፡- ኧ!!! ...ሌላ ደሞ ምን ነበር? አዎ! እያመሸህ መግባት አትችልም*

*እሱ፡- እሺ እሷ፡ እም...ሌላ? ሌላ? ምንድነው የረሳሁት? ሌላ የምትተወው ነገር ምን ነበር?*

*እሱ፡- አንቺን ማግባት ( ፌስ ቡክ፤ ኮተቤ ፕረስ)*

ሰዎች ወደጋብቻ ከመግባታቸው በፊት በወደፊት ህይወታቸው ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው፣ ያቅዳሉ ይመካከራሉ፡፡ በሴቷም ሆነ በወንዱ በኩል በትዳር በሚኖሩበት ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ

ችግሮችና መፍትሄያቸው ውይይት ሊደረግባቸውም ይገባል። በዚህኛው ቀልድም ይህ ተሞክሮ ይታያል። ይሁንና ዕቅዱ የአንድ ወገን ስልጣን የሚታይበት ነው። በቀልዱ ሴቷ በማግባባት ሳይሆን በስልጣን ድምፅ ከሰውየው የማትፈልጋቸውን ፀባዮችን እንዲተው ታዝዘዋለች። ወንዱ አይ አልተውም አላላትም። በሀሳብዋ የተስማ መስሎ ፍላጎቷን ሲያዳምጣት ቆይቷል። ነገር ግን በመጨረሻ የሚያሰማት ውሳኔ እሱ እስዋን ከመጠጥና አምሽቶ ከመግባት በላይ የማይወዳት መሆኑን የሚያሳይ ነው። በእርግጥ በሴቷም በኩል ቢሆን አልፈልጋቸውም የምትላቸውን ፀባዮቹን ለማስተው ስታግባባው አናይም። ይልቁንስ ከፍቅር ይልቅ ክብሯን አስበልጣለች። ይህንኑም ባልሆነ መንገድ ስትገልፀው ትታያለች። በዚህ ቀልድ ውስጥ የምናየው በጥንዶች መካከል ፍቅር የሌለ መሆኑን ነው። ወንዱ ሴቷ የማትፈልጋቸውን ፀባዮች ለመተው የተስማማ ቢመስልም ልምዶቹን ከመተው ይልቅ እስዋን መተው እንደሚቀለው በውሳኔው ይገልፃል። ይህም በመካከላቸው ያለው ፍቅር የውሸት መሆኑን ወይም በመካከላቸው ፍቅር የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

1. *ባልና ሚስት እየተደባደቡ እዚህ ቤት ደህና ዋላችሁ የሚል ድምፅ ስለሰሙ አቤት ማን ነው ይግቡ ይላሉ። ከዚያ ሰውዬው ጉዳዩን ጨርሶ እስኪወጣ የእኔ ፍቅር የእኔ ማር እየተባባሉ ይቆያሉ። እንግዳው ቤቱን ለቅቆ እንደወጣ ባልዬው በይ ካቆምንበት እንቀጥል አላት።*

ይህ ቀልድ ፍቅር ሳይኖራቸው ፍቅር እንዳላቸው የሚያስመስሉ ባልና ሚስትን ታሪክ ይገልፃል። ባልና ሚስቱ አይዋደዱም፣አይከባበሩም፣ይህም እርስ በእርሳቸው የሚደባደቡ መሆናቸውን በማየት መረዳት ይቻላል። በባልና ሚስት መካከል ጥል አለ። ጥሉም እስከድብድብ የሚደርስ መሆኑን እናያለን። ነገር ግን እነዚህ ባልና ሚስቶች በፍቅር ካለመኖራቸው በላይ በእውነተኛ ማንነታቸው የማይኖሩ ናቸው። ይልቁንስ ለውጪ ሰው እንደሚዋደዱ እያስመሰሉ ይኖራሉ። ስለዚህም ትዳሩ ከጋብቻ እሴቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ፍቅር የሌለበት ነው። ፍቅር ባለመኖሩም ድብድብ፣ አለመከባበር፣ ይቅር አለመባባልና፤ ውሸታምነት በትዳሩ ውስጥ ይታዩበታል።

2. *ሚስት አምሽታ ወደቤት እየገባች ነው ወድያው የመኝታ ቤቷን ከፍታ ስትገባ አልጋዋ ላይ ሁለት የተኙ ሰዎችን ትመለከታለች፤ አራት እግሮች ከብርድ ልብሱ ስር ወተው ይታያሉ ከዝያም ወድያውኑ አጠገቧ ያለውን ዱላ አንስታ ከብርድ ልብሱ ውስጥ ያሉትን ሁለቱን ሰዎች ባላት ኃይል መደብደብ ትጀምራለች ..ወድያው መደብደቡን ታቆምና ወደ ሳሎን ቤት ስትሄድ ባሏ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነብ ነበር ከዝያም ባልየው " hi darling...ቤተሰቦችሽ መተዋሉ የኛ መኝታ ቤት ተኝተዋል ሰላም አልሻቸው ..?ሲላት ሚስት በድንጋጤ እራሷን ስታ ወደቀች። "የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል አሉ" yaskal.wordpress.com/2016/02/08*

በዚህኛው ቀልድ ውስጥ የምናየው ሚስት ባልዋን የማታምን መሆኑን ነው። ሴትዮዋ ከቤት እንደገባች አልጋዋ ላይ የተኛ ሰው በማየትዋ ባልዋ በእስዋ ላይ እንደወሰለተ

ነው የምትረዳ፡፡ በቀልዱ ባልየው ሚስቱን የሚያከብር መሆኑ ይታያል፡፡ ሚስቱን የሚያከብር በመሆኑ የሚስቱን ወላጆች አልጋውን ለቅቆ እንዳስተኛቸው እናያለን፡፡ በአንፃሩ ሚስት ባሏን እንደማታምነው ይታያል፡፡ በአልጋዋ ላይ ሰዎች ተኝተው ስታይ ጉዳዩን ለማረጋገጥ ምንም ሳትሞክር የጭካኔ እርምጃ ትወስዳለች፡፡ በዚህ እርምጃዋም ለእንግድነት የመጡ የገዛ ወላጆችዋ ላይ ጉዳት ታርሳለች፡፡ ጉዳት ያደረሰችው በወላጆችዋ ላይ መሆኑን ስታውቅ ደግሞ ራስዋን ትስታለች፡፡ ይህ ያለማመንዋ ውጤት ነው፡፡

3. *ሚስት አምስት አንድ አይነት ፓንት ገዝታ ለባሏ ትሰጠዋለች፡፡ ለምን አንድ አይነት ገዛሽ አሁን ሰዎች የማልቀይር ይመስላቸዋል፡፡ ይላታል፡፡ ሚስት ፈጠን ብላ እኮ እነማን ናቸው የማትቀይር የሚመስላቸው ስትል አፋጠጠችው፡፡ ባል በልቡ ወይ መበላት እያለ ነው፡፡*

   በዚህ ቀልድ ውስጥ ሚስት ለባሏ አሳቢ መሆንዋን ባል ግን ታማኝ አለመሆኑን እናያለን፡፡ ሚስት ባልዋን ለመንከባከብ ያደረገችው ሙከራ የባሏን አመንዝራነት ያሳያታል፡፡ ይህም በትዳሩ ውስጥ አለመተማመን መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ቀልድም በትዳር ውስጥ ያለን አለመተማመን ያሳያል፡፡

4. *አንድ ጎልና አንድ ሚስት አያስተማምንም ያለው ልጅ፤ ሚስቱ አንድ ጎልና አንድ ባል አያስተማምንም ብትለውስ?*

በዚህ ጥቅስ መሰል ቀልድ ምንም እንኳን ትዳር በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ሊመሰረት የሚገባው እነዚህ ሰዎችም መዋደድን፣መተማመንንና መከባበርን እሴት አድርገው መኖር የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ወንዱ አንዲት ሴት አምኖ መኖር አስተማማኝ አይደለም የሚል አስተሳሰብ እንዳለው ያሳያል፡፡ ለዚህ አስተሳሰቡም የእግር ኳስ ጨዋታን ማሳያ አድርጎ አቅርቧል፡፡ በእግር ኳስ ጨዋታ አንድ ጎል ብቻ ያስገባ ቡድን በማንኛውም ደቂቃ ጎል ሊገባበት ና ውጤቱ ሊቀየር እንደሚችል ሁሉ፤አንድ ሚስት ያለችው ሰውም ምናልባት ሚስቱ ትታ ብትሔድ ወይም ብትሞት ብቸኛ ላለመሆን ሲል በህይወቱ ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ ሴቶች እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ በዚህ አስተሳሰቡም ምናልባት ከሚስቱ ውጪ ከሌሎች ሴቶች ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሀሳብ አለው፡፡ ነገር ግን ቀላጁ ወንዱ ይህንን እንዳለው ሁሉ ሴቷ ያንን ብትል ትዳር ምን መልክ ይኖረዋል? የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ በባልና ሚስት መካከል የሚኖር አለመተማመንና አለመዋደድ የትዳርን መልክ ሊያጠፋ የሚችል መሆኑ ይጠቁማል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ክፍል የቀረቡት ቀልዶችን መሠረት በማድረግ ከተደረገው ትንተና አሁን ላይ በትዳሮች መካከል መከባበርና መተማመን የሌለ ከመሆኑ ባሻገር ትዳሮች ፍቅር የሌላቸው፤ ፍቅር ያለበት የሚመስለውም ቢሆን የማስመሰል ፍቅር መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ቀጥሎ በትዳር ውስጥ የባልና ሚስት ሚና ምን መልክ እንዳለው የሚያሳይ ትንተና ቀርቧል፡፡

### 2.3. በትዳር ውስጥ የስነፆታ ሚና

በሌቪ ስትራውስ የሚቀነቀነው መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ ተፈጥሮ በአቻ ተቃርኖዎች የቆመች እንደሆነች ይገልፃል፡፡ ይህንንም በባህል ውስጥ እንደምናገኘውና ባህል እንዴት አድርጎ ሀሳቦችን በተለይ በአቻ ተቃራኒነት እንደደለደላቸው መፈለግ እንደሚቻል ያሳያል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የትዳርን አፈጣጠር ስናይ ሴትና ወንድ ወይም ባልና ሚስት በሚሉ ሁለት አቻ ተቃራኒዎች መገንባታቸውን እንመለከታለን፡፡ ትዳር በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት ባልና ሚስት የመሆን ፍላጎትና ቤተሰብ የመመስረት ነጻ ፍላጎት የሚመሰረት ተቋም ነው (Stewart, 2006)፡፡ ይህ ተቋም ከተመሰረተ በኋላ ባልና ሚስት እንደአንድ ሰው ይኖራሉ፡፡ ትዳር የተመሰረተበት አንዱ አላማ መተጋገዝ ነውና የትዳር ሕይወቱን እየተጋገዙ እንደአንድ ሰው ይመሩታል፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት 1993፣217) እንደሚገልፀው ትዳር ‹‹ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው እንዲኖሩ የሚያስችላቸው፣ በቃል ኪዳን የታሰረና ህጋዊ የሆነ ጥምረት፣ አንድነት፤ የባልና ሚስት የአንድነት ኑሮ፤ ትዳር፣ ቤት፣ ንብረት፤ ባል ወይም ሚስት›› ማለት ነው፡፡ ይሁንና ባልና ሚስቱ ትዳሩን በአግባቡ ለመምራት ያስችላቸው ዘንድ ሴቷም በሴትነቷ ወንዱም በወንድነቱ ሊጫወቱት የሚገባ የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡

እነዚህ ሚናዎችም ባህላዊና ማህበራዊ አውድን መሠረት አድርገው የተፈጠሩ ብሎም ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአማርኛ ተናጋሪው ማህበረሰብ ከሀይማኖትና ባህል በተቀዳ ነባር ልማድ መሠረት ሴት ለባሏ መታዘዝ ሚናዋ ሲሆን፣ ወንድ ደግሞ በፍፁም ልቡ ሚስቱን መውደድ (ፍቅር የሚሰጣቸውንና የሚጠይቃቸውን ሀላፊነት መሸከም) ሚናው ነው፡፡

በኢትዮጵያውያን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ባህል ደግሞ ወንድ ገንዘብ በሚያስገኙና ጉልበትን በሚጠይቁ ተግባራት ላይ የመሰማራት፣ ቤተሰቡን የመጠበቅ ሚና ሲሰጠው፣ ገቢ በሚያስገቡ ስራዎች ላይ የተሰማራች ብትሆንም እንኳን የቤት ውስጥ ስራዎችን መስራት፣ ቤተሰቡን መንከባከብ የሚስት ስራ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ይዘን የባልና ሚስት ሚና በቀልዶች እንዴት ተገልጧል ስንል የሚከተለውን ሁኔታ እናያለን፡፡

1. *ሚስት የቤት ውስጥ ስራ በጣም በዝቶባት አንዱን ስትል አንዱ እየተደራረበባት ሳታርፍ ቀኑ ይመሻል፡፡ ባል ሆዬ ቤት ሲገባ መብላት መጋደም ነው ስራው፡፡ ከስራ ሲመጣ ጠብቃ፡-*

   *ሚስት፡ - እስቲ የኔ ውድ የውጭው በር ተሰብሯል ስራልኝ ስትለው*

   *ባል፡ - አቦ ደክሞኛል ስታይኝ አናፂ እመስልሻለሁ እንዴ ! ብሎ ሳይሰራላት በቁጣ*

   *ይወጣል ፡፡በነጋታው ደሞ መብራት ይቃጠልባት እና ሲመጣ*

   *ሚስት፡ - ውዴ የሳሎኑ መብራት ተቃጥሏል እስኪ ቀይረው ስትል*

   *ባል፡ - ስታይኝ ቴክኒሻን እመስላለሁ እንዴ ብሎ አሁንም ሳይቀይርላት አመናጭቋት ወጣ*

   *ከዛም በሌላ ቀን ባል ከስራ ሲገባ በሩ ተሰርቶ አንፓሉም ተቀይሮ ቤቱ ፏ ብሎ*

   *ጠበቀው፤-*

*ባል፡ - ማነው ባክሽ እንዲህ ያስተካከለው አላት፤*
*ሚስት፡ - አንዱ ሰውዬ እሚሰራልኝ አጣሁ ብዬ ሳወራ እኔ አስተካክልልሻለሁ ግን ዳቦ*
*ከጋገርሽልኝ ወይም አብረሽኝ ከተኛሽ ነው አለኝ ስትለው*
*ባል - በንዴት እና ዳቦ ጋገርሽለት ይላታል*
*ሚስት - እንዴ ስታዬኝ ዳቦ ጋጋሪ እመስላለው! (ፌስ፣ ቡክ)*

በዚህ ቀልድ ውስጥ በባልና ሚስቱ መካከል ሚናን ያለመወጣት ተግባር ይታያል፡፡ በቀልዱ ባልዬው የራሱን ሚና መወጣት አቅቶት ሚስቱን ወደጥፋት ሲመራት እናያለን፡፡ ሚስት በቤት ውስጥ ብርቱ ጫና አለባት፡፡ ባል ግን የሚስቱን ሁኔታ ተረድቶም ሆነ ማህበረሰብ የጣለበትን ሚና ተቀብሎ መከወን አልፈለገም፡፡ ከእሱ የሚጠበቀውን ሀላፊነት የመወጣት ፍላጎት የለውም፡፡ ይህንን ጊዜ የባሏን ክፍተቶች ለመሙላት የታገለችው ሴት ሌላ አማራጭ ትከተላለች፡፡ ያ አማራጭ ግን በባልና ሚስቱ መካከል ሊኖር የሚገባውን መተማመን የሚያፈርስ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ቀልድ ደግሞ በማህበረሰብ ደንብ ውስጥ የተለመደውን የባልንና ሚስትን ሚና አለዋውጦ ያቀረበ ነው፡፡

2. *ሚስት ትደውልና የማትረባ ደደብ የት አባክ ነው ያለከው*

*ባል ፡- ፒያሳ ነኝ*

*ሚስት፡- እዛ ምን ትሰራለህ?*

*ባል፡- እንዴ ትዝ ካለሽ የሆነ ወርቅ ቤት አልነበኘንም?*

*ሚስት፡- አስታወስኩት ውዴ*

*ባል፡- የወርቅ ሐብል አይተሽ ወደድኩት ስትይ ገንዘብ ሳገኝ እገዛልሻለሁ*

*አላልኩሽም?*

*ሚስት፡- አዎ የእኔ ፍቅር፤*

*ባል፡- ወርቅ ቤቱን አወቅሽው?*

*ሚስት፡- አዎ ወለላዬ*

*ባል፡ ከእሱ አጠገብ ያለው ግሮሰሪ ነኝ (ፌስ ቡክ፤ኮተቤ ፕረስ)*

በቀልዱ ሚስት ባሏን ባልተገባ የንግግር ሁኔታ ልትቆጣጠረው ስትሞክር ትታያለች፡፡ ሚስት በልማዳዊው አኗኗር ሴቶች በተለይም ስርዓት ያላቸው የሚባሉት ሲሉ በማይጠበቁበት መንገድ ‹‹የማትረባ ደደብ የት አባክ ነው ያለከው›› ብላ ትጠይቃለች፡፡ ይህንን ጊዜ ባል የሚስቱን ቁጣ የሚበርድበት መላ ይመለምላል፡፡ ወርቅ ሊገዛልኝ ነው ብላ እንድታስብ ያደርጋታል፡፡ ሚስት ይህንን በማሰብዋ ከቁጣዋ በርዳ ባሏን አቆላምጣ ትጠራዋለች፡፡ ይሁንና ባልዋ አድራሻውን ለመግለፅ የተጠቀመው መንገድ ከሚስት ቁጣ የማምለጥ እንጅ እውነተኛ አይደለም፡፡ በዚህ ቀልድ ውስጥ ሚስት ባሏ የሚፈራት ባለጉልበት፣ ባል ደግሞ ፈሪ ሆኖ ተስሏል፡፡ ይህም ትዳር ውስጥ የነበረውን ልማዳዊ የባልና ሚስት ባህርይ መቀያየሩን የሚያሳይ ነው፡፡

3.*በአንድ የስነፆታ እኩልነትን ርዕሰ ጉዳዩ አድርጎ ለወንዶች ስልጠና ለመስጠት በተሰናዳ ሰብሰባ፣ ሰብሳቢው እስኪ በትዳራችሁ ውስጥ ደስተኛ የሆናችሁ፣ በትዳራችሁ ውስጥ የሚያጋጥሟችሁን ችግሮች ከሚስቶቻችሁ ጋር በመነጋገር እየፈታችሁ ትዳራችሁ እየመራችሁ*

*ያላችሁ ሰዎች ምን ያህል ናችሁ ሲል ይጠይቃል። ተሰብሳቢዎች ዝም ይላሉ። እሽ ተመካክረን ነው የምናድር የምትሉ ከወንበራችሁ አትነሱ፡ አይ አንመካከርም ወይ እስዋ ወይ እኔ እንወስናለን የምትሉ ደግሞ ከወንበራችሁ ተነሱና ቁሙ ይላል። ይህንን ጊዜ ሁሉም ተሰብሳቢ ተነስቶ ይቆማል። አንድ ሰው ብቻ እንደተቀመጠ ይቀራል። ሰብሳቢው በጣም ይገረምና አንድ ሰው ብቻ ነው ከሚስቱ ጋር የመመካከር ልምድ ያለው? ካለ በኋላ፤ እሽ ይህንን ልምድ እንዴት አዳበርከው? እስኪ ልምድህን ንገረን ይለዋል። ሰውዬውም መመካከር? የምን መመካር? ኧረ እኔ ትናንትና ማታ ለምን አስተያየት ሰጠከኝ ብላ ጎኔን በዘነዘና የመታችኝ አላስቆመኝ ብሎ ነው ተቀምጬ የቀረሁት አለ። (አሰፋ አበጋዝ፣10/05/2017፣ባሕር ዳር)።*

በዚህ ቀልድ ውስጥ የታየው ሀሳብ በብዙ ትዳሮች ውስጥ መመካከርና መከባበር የሌለ መሆኑን የሚጠቁም ነው። ከዚህም በላይ ሴቶች ባልተለመደ ሁኔታ በወንዶች ላይ አካላዊ እርምጃ ሲወስዱ ይታያል። ይህም በእንስታዊ አተያይ ‹‹ባህል ሴቶችን ተጨቋኝ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል›› የሚለውን አባባል ሲታገል እናያለን። የዚህ ቀልድ አሳቂነት የሚመነጨውም ከዚሁ ከሁለቱ ሀሳብ ተቃርኖ ነው። ንድፈ ሀሳቡና ነባር ልምዱ የሚነግሩን ጠብና ድብድብ ባለበት ትዳር ውስጥ በአካላዊ ጥንካሬ መመካት እንበል መደባደብ የወንዶች መገለጫ መሆኑን ነው። ይሁንና በዚህ ቀልድ ውስጥ ሴቷ ደብዳቢ ወንዱ ደግሞ ተደብዳቢ ሆነው እናገኛለን። ይህም የሚና ለውጥ የሚያሳይ ነው።

## 3. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ትዳርን አስመልክቶ የሚነገሩ ቀልዶችን ይዘት መመርመር ነበር። በዚህ ዋና ዓላማ ስር በቀልዶች አማካኝነት የተገለፀው የትዳር ብያኔ ምንድን ነው? ቀልዶች የትዳር እሴቶችን እንዴት አቅርበዋቸዋል? ቀልዶች በትዳር ውስጥ የስነፆታን ሚና እንዴት ይገልፁታል? የሚሉ ጥያቄዎች በንዑስ ዓላማነት ተዘጋጅተው ነበረ። ጥናቱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተገቢ ያለውን የምርምር ሂደት የተከተለ ሲሆን ከመረጃ ትንተናው ትዳር የመከራና የስቃይ ቦታ የሚል ትርጉም እየተሰጠው ነው፤ መፋቀር፣መተማመንና መከባበር የተባሉ የትዳር እሴቶች እየፈረሱ ነው፤ በትዳር ውስጥ የባልና የሚስት ስነፆታዊ ሚና እየተቀየረ ነው፤የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል። ከውጤቶች በመነሳትም የቤተሰብ ብሎም የሀገር ግንባት መሠረት የሆነው ትዳር መዋቅሩ እየተናጋ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። ከድምዳሜው በመነሳትም ጥሩ ሀገር የጥሩ ቤተሰብ ውጤት ነውና ሌሎች አጥኝዎች ሰፊና ተከታታይ ምርምሮችን በመስራት የመፍትሔ ሀሳቦችን ቢጠቁሙ፣የማሕበረሰብ ህልውና ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ጥሩ ቤተሰብ መገንባት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ቢረባረቡ ዛሬ እየደረሰ ያለውን ምስቅልቅልና ነገ ሊደርስ የሚችለውን የሀገር መፍረስ አደጋ ለመከላከል ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል የሚል የይሁንታ ሀሳብ ተሰጥቷል።

**ምስጋና**

ይህ ጥናት ውጤታማ ይሆን ዘንድ መረጃ በመስጠት ያገዛችሁኝ የመረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## 4. ዋቢዎች


መልሰው በሪሁን፡፡ (2012 ዓ.ም)፡፡ ጥርጣሬ፡- በፌስቡክ ቀልዶች ውስጥ. በፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰርካለም በሪሁን፡፡ (2011)፡፡ "ወቅታዊ" (ከመጋቢት 2010 - መጋቢት 2011) የፌስቡክ ፖለቲካዊ ቀልዶች አውዳዊ ይዘትና እንድምታ፡፡ በፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

አፈወርቅ ተፈራ፡፡ (2009 ዓ.ም)፡፡ የሰርግ ስነ ስርዓት ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ በሃራና አካባቢው ማህበረሰብ፡፡የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋካሊቲ፣ ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል፣ ባሕርዳር፡፡

ገነት ስመኝ፡፡ (2012 ዓ.ም)፡፡ ፣በባህላዊ የትዳር ሥርዓት ውስጥ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች አንድምታና ፋይዳ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ. በፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ጠና ደም፡፡ (2008*)፡፡ ሰው፣ግብረገብና ስነምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች*፣አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ፕረስ፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ (1980 ዓ.ም) ፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

*የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡(1993 ዓ.ም)፡፡ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ድሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ህግ፡፡ (1995)፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ:: (1962 ዓ.ም.)፡፡ *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ *የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዝናሽ ሰለሞን፡፡(2004 ዓ.ም)፡፡ የሀድያ ብሄረሰብ የባህላዊ ትዳርና የሰርግ ስነ ስርዓት፡፡ ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ፡፡

Ahuja, V.and Bali, T. (2018). What makes us laugh? Investigations into Automatic Humor Classification. *Proceedings of the 27th International Conference on Computational Linguistics*.https://www.researchgate.net/publication/325447085. DOI:10.18653/v1/W18-1101

Attardo, S. (1994). *Linguistic Theories of Humor*. Mouton de Gruyter.

Bergson H. (2003). Laughter. *An Essay on the Meaning of the Comic*. [EBook #4352], ISO-8859-1

Darwin, C. (2003). *The origin of species: A facsimile of the first edition*. Harvard University Press.

Davis, S. M. (1993) .What's So Funny?: *The Comic Conception of Culture and Society.* University of Chicago Press.

Gary S. B.(2014). *A theory of marriage* (part 2); the University of Chicago Press.

Monte N. S. Jacob D. B, and Julie S. (2012). Marriage, Fundamental Premises, and the California, Connecticut, and Iow a Supreme Courts. https://digitalcommons.law.byu.edu/lawreview/vol2012/iss1/4

Morreall, J. (1983). *Taking Laughter Seriously*. SUNY Press.

Perkins, C. (2023). What is Funny? Writing about, reading, and researching humor. Tulsa Community College.

Rayn T E. and Robert P. G. (2012). Harvard Journal of Law & Public Policy 34(1) Https://www.researchgate.net.

Viriya j, (2015). Styles and types of humor and virality of memes of Facebook, volume 10 issue; 3 page(s) 288-302 article first published online:

**ወቅታዊ ዝግጅት፣ የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ነው በሚል ርዕስ የቀረበ ውይይት፣**(2008) **ነሐሴ** 04/**ዓ.ም፣**/1227152770649930. https://web.facebook.com/EBCzena/videos

https://amharic.voanews.com/a/7227932.html

https://am.al-ain.com/article/basic-concerns-before-you-get-marry

Claude-Levi-Strauss. Last Updated:Jan 8, 2025.Https://www.britannica.com/biography/

Stewart (2006) https://www.Dictionary.Com).

(https://www. dmeyesus. org/wedding).

https://yaskal.wordpress.com/2016/02/08bd-amharic-jokes/.

https://yihune88.wordpress.com/2015/07/26.